በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቀን ሐዳር 2 5 2012
Date
ቁጥር 6/0167/12
Ref.No.

የጉምሩክ ስነስርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
ባሉበት

ጉዳዩ፡- ከቀረጥ ነፃ የገቡ ተሽከርካሪዎችን ይመለከታል፡፡

በኤምባሲዎች፣ አለም አቀፍ እና አህጉራዊ ድርጅቶች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ አገር ውስጥ ገብተው የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ወደሌላቸው ሶስተኛ ወገን የሚተላለፉ ተሽከርካሪዎች በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የሽያጭ ውል ተደርጎ ቀረጥና ታክስ ለመክፈል ወደ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ሲቀርቡ በመመሪያ ቁጥር 3/1996 የእርጅና ቅናሽ እየታሰበ ለበርካታ ዓመታት ሲሰራበት ቢቆይም የእርጅና ቅናሽ የቀን አወሳሰድን አስመልክቶ በተለያየ ጊዜ የተለያየ ማብራሪያ የተሰጠ በመሆኑ ማለትም ተሽከርካሪውን በተሻሻጡበት ወቅት ባለው ዋጋና ምጣኔ እንጂ ዲክላራሲዮን ሞልተው በቀረቡበት ቀን መሆን እንደሌለበት በቀድሞው የጉምሩክ ኦፕሬሽን ዋና ስራ አስኪያጅ ማብራሪያ መሰጠቱ እንዲሁም በተሽከርካሪው ላይ ቀረጥና ታክስ ለመክፈል ለባለስልጣኑ ያሳወቅበትን ቀን ዕቃው እንደተላለፈበት ቀን መውሰድ የተሻለ እንደሆነ የህግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት የዋና ዐቃቤ ህግ ደብዳቤ በመጥቀስ ያስተላለፈው ሁለቱም የተለያዩ ስለሆኑ የትኛውን መውሰድ እንዳለባቸው አቅጣጫ እንዲሰጥ የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በቁጥር 3.1/ደ43/399 በቀን 8/3/2012 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ መጠየቃቸው ይታወሳል፡፡

ስለሆነም ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ አገር ውስጥ ገብተው ለሶስተኛ ወገን ሲተላለፉ ቀረጥና ታክስ ለማስከፈል የእርጅና ጊዜው ሽያጩ ከተከናወነ ከ6 ወር በላይ አዘግይተው ለሚቀርቡ ሽያጭ ስምምነት እስከተገባበት ጊዜ ድረስ ብቻ እንዲታሰብ እንዲሁም የሽያጭ ስምምነት በተገባ እስከ 6 ወር ጊዜ ለሚቀርቡ ዲክለር እስከተደረገበት እየታሰበ እንዲሰራ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሙሉው ሚኤ አበበ
የጉምሩክ ኦፐሬሽን
ዘርፍ ም/ኮሚሽነር

ግልባጭ/
- ለጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለዋጋ ትመናና ልማት ዳይሬክቶሬት
  ጉምሩክ ኮሚሽን

ለዘመናዊና ፍትሀዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

☎ +251 116 62 98 00
+251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia